ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

”የፍቅር ጥግ ፊልም ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር"

ማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ለባችለር ኦፍ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ

ግንቦት 2014 ዓ.ም

"የፍቅር ጥግ ፊልም ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል ደረጃ አንፃር"

በ

እዮብ ታምሬ

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ሳራ መሃመድ

ማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ለባችለር ኦፍ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ

ግንቦት 20

የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩነቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም ሳራ መሃመድ
ፊርማ_____

ይህ በተማሪ እዮብ ታምሬ "የፍቅር ጥግ"ፊልም ከገጸባህርያት አሳሳል አንፃር የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆንየዩንቨርስቲዉ ጥራት ደረጃ የሚላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆነን ማረጋገጫ ነዉ።

ፈታኝ አንድ ----------ፊርማ
ፈታኝ ሁለት----------ፊርማ

ቀን ----------

ምስጋና

በመጀመሪያ ፈጣሪ ባንተ እርዳታነት ነው ሁሉም የሆነው እና እግዚአብሔር ሆይ ምስጋና ላንተ ይሁን። በመቀጠልም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በመከታተል በቅንነት አብራኝ ለነበረችው መምህርት ሳራ መሃመድ ምስጋናዬ እና አክብሮቴ የላቀ ነው።

አበርክቶ

በሁሉም ነገር ለምትረዳንኝ ወልዳ አሳድጋኝ ለዛሬዉ ቀን እንድበቃ እንደ እናትም እንደ አባትም ሆና ላሳደገችኝ ለምወዳትና ለማከብራት ለዉዷ እናቴ ይሁንልኝ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የፍቅር ጥግ ፊልም ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል ደረጃ አንፃር የሚያቀርብ ነው። ጥናቱ የተሰራበት ዘዴም ገላጭ ሲሆን የተጠቀመው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ፊልሙን በመመልከትና ተያያዥነት ያላቸውን ፅሁፎች በማንበብ ነው። ጥናቱ የሚያነሳቸው ሀሳቦችም በሚተውኑት ገፀ-ባህሪያት ከፍቅር ጥግ ፊልም ጋር በማጣመር የገፀ-ባህሪያትን ድክመት እና ጥንካሬ ለማሳየት የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ማውጫ

ምስጋና I

አበርክቶ II

አጠቃሎ III

ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.2 የጥናቱ አላማ 2

1.2.1 የጥናቱ አብይ አላማ 2

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን 3

1.5.የጥናቱ ዘዴ 3

1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 3

1.7 የጥናቱ አወቃቀር 3

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 4

ምዕራፍ ሁለት 5

2. ክለሳ ደርሳናት 5

2.1 የፊልም ምንነት 5

2.2 የገፀ-ባህርይ ምንነት 6

2.3 ገፀባህርይ የሚሳሉበት መንገድ 7

2.3.1 አካላዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ደረጃ 7

2.3.2 ማህበራዊ የገፀ-ባህረ አሳሳል ደረጃ 8

2.3.3 ስነ-ልቦናዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል 8

2.3.4 ግብረ-ገባዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል 9

ምዕራፍ ሶስት 11

3. መረጃ ትንተና 11

3.1 የፍቅር ጥግ ፊልም ታሪክ 11

3.1 የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ-ባህሪያት አሳሳል 13

ምዕራፍ አራት 25

4. ማጠቃለያ 25

ዋቢ መፅሐፍት 26

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

ፊልም ታሪክን በምስልና ድምፅ ጎብር የማሳያ እና የመንገሪያ ጥበብ ነው። ይህ አይነቱ ታሪክን የመንገሪያ ጥበብ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ለመድረስ ከመቶ አመታት በላይ ታሪካዊ የለውጥ ሂደቶችን አሳይቷልአዲስ ተስፋ “የፊልም ድርሰት አጻጻፍ ብልሃት” በሚለዉ መጽሃፉ ላይ እንዲህ ሲል ገልጿል። ፊልም ታሪክን በምስል የመናገር ጥበብ የተጀመረው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1890 አከባቢ ነበር። መሰረቱን ከመቅረጫ መሳሪያዎች አድርጎ የተነሳው የፊልም ጥበብ እስከ 1910 እ.ኤ. ድረስ ሲኒማቶግራፈር እና ዳሬክተር ባላሙያዎችን ብቻ በመያዝ ከዛምተዋናዮችን በማሳታፍ ድምአ በሆነ መልኩ ታሪክ መንገሩን እስከ 1927 እ.ኤ.አ ድረስ ቀጠለ። በዚህ ድምፅ አልባ የፊልም ጥበብ ውስጥ ትልቅ ስም ያለው ቻርሊ ቻፕሊን ነው። ከዚህ በኋላ በ1929 እ.ኤ.አ ገደማ ድምፅ መቅረጫ በመፈጠሩ ምስልና ድምፅን በማቀናጀት ታሪክ የመንገሪያ ጥበብነቱን አወጀ። ፊልም አንድን ታሪክ የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም የተለያዩ ሀሳቦችን የምናነሳበት፣ ታሪክን የምንፈጥርበት እና የምናቀርብበት አንዱ መንገድ ነው። የሰው ልጅ ማህበራዊ ማንነትን፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን እንዲሁም የሰብዓዊ ገጠመኝ መሰረት ያደረገ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ የሚታየውን እና የማይታየውን አለም ገልጦ የሚያሳየን ነው። ፊልም ታሪክን በምስል ድርጊትን በእንቅስቃሴ የመንገር እና የመግለጽ ጥበብ አለው። እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታውን ወይም ተስጦውን የሚገልጽበት ነው። በሌላ በኩል የአንድን ሀገር ባህላዊማህበራዊ፣ እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎችን የምንገልጽበት ነው። ፊልም ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ እየተሰራ የሚገኘው ተንቀሳቃሽ ምስል ከመጣ ብኋላ ነው። እንዲሁም ፊልም ምስላዊ በመሆኑ የምንመርጠውን ታሪክ ወይም ሃሳብ ለተመልካች ግልጽ በሆነ መንገድ ማሳየት ይኖርብናል። “(2005፤34)

በሀገራችን ኢትዮጵያ በቁጥር ትንሽ የማይባሉ በርካታ ፊልሞች ተሰርተዋል። ከነዚህም በርካታ ፊልሞች መካከል አንዱ የሆነዉ ”የፍቅር ጥግ ፊልም ነው። ”የፍቅር ጥግ ፊልም ደራሲ መስተጃብ ዴታም ፣ዝግጅት በፍቃዱ ከበደ እና በሳልቃን ፊልም ፕሮዳክሽን 2013 ዓ.ም ለተመልካች የቀረበ የኢትዮጵያ ፊልም ነዉ። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የፍቅር ጥግ ፊልምን ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር መተንተን ላይ ያተኮረ ነው።

1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኚዉ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳዉ የፍቅር ጥግ ፊልም ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር የተሰራ ምንም አይነት ጥናታዊ ፅሁፍ ባለመሰራቱ እና የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ-ባህሪያትን አሳሳል አነፃር በትክክል ለመመልከት እንዲሁም የበኩሉን አስተወፆ ለማበርከት በማሰብ ነዉ። እዲሁም ደግሞ ፊልሙን ደጋግሞ በመመልከት ሌላዉ ሰው ያላወቃቸውን ጉዳዮች በጥልቀት እንዲመለከት የደርጋል።

1.2 የጥናቱ አላማ

1.2.1 የጥናቱ አብይ አላማ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አብይ አላማ የፍቅር ጥግ የተባለውን ፊልም ከገፀ-ባህሪ አሳሳል አንፃር መተንተን ነው።

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ✓ የፍቅር ጥግ የአማርኛ ፊልም ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር ጠንካራ እና ደካማ ጎን በማውጣት ወደፊት ጥሩ የገፀ-ባህሪያት አሳሳል እንዲኖር ያደርጋል።
- ✓ የገፀ-ባህሪያትን ችግሮች በማውጣት ወደፊት ለሚሰሩት ፊልሞች ወደ ተሻለ መፍትሔ እንዲሄዱ ይረዳቸዋል።
- ✓ የፍቅር ጥግ በተሰኘዉ ፊልም ላይ ያሉትን የገጸባህሪያት ከገጸባህሪያት አሳሳል አንፃር በማየት የገጸባህሪያቱን ሙሉ ማንነት ማሳወቅ ነዉ።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

- ✓ ስለ ፊልም ገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር ያሳውቃል
- ✓ የገፀ-ባህሪያት አሳሳልና ሊኖራቸው የሚገባ ሚና ለማያውቁ ግንዛቤ ይሰጣል
- ✓ በትወና ሙያ ወይም በድርሰት እና በዝግጅት ላይ ያሉ ባለሙያዎችን የተሻለ ገፀ-ባህሪ በተመለከተ

  ስራ እንዲሰሩና ስህተት ካለባቸው እንዲያስተካክሉ ሌሎች ስራዎቻቸውንም እንዲገመግሙ መንገድ ይከፍታል
- ✓ በትያትር ጥበባት የመጀመሪያ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስችሉ መስፈርቶች አንዱን ለማሟላት

1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የፍቅር ጥግ የተሰኘዉ ፊልም ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር የሚዳሰስ ነው

1.5.የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የሚባል ጥናታዊ ፅሁፍ አይነት ሲሆን አጥኚዉ የመረጠዉ ዘዴ በገፀ-ባህሪ አሳሳል ዙሪያ የተፃፉ ፅሁፎችን በማንበብ እና የፍቅር ጥግ ፊልምን በደንብ በመመልከት ነዉ። አጥኚዉ የተሰማዉን ሀሳብ ለማብራራት የተጠቀመዉ ዘዴ ስለገፀ-ባህሪያት አሳሳል ይተነትናል። ያለዉ እንዳዉቅ ''የምርምር መሰረታዊ መረሆችና አተገባበር '' (2009፣21) በሚለዉ መጽሃፍ ዉስጥ ስለ ገላጭ ምርምር እንዲህ ሲል ያትታል "ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተዉ ተመራማሪዉ አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ነዉ። አጥኚዉ ይህንን ገላጭ የጥናት አይነት በመጠቀም "የፍቅር ጥግ" ፊልም ከገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር ምን ይመስላሉ የሚለዉን የሚተነትን ንዉ።

1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ✓ የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ-ባህሪያት ከገፀ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር ሲተነተኑ ምን ይመስላሉ?
- ✓ የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ-ባህሪያት ጠንካራ ጎን እንዲሁም ደካማ ጎን ምን ይመስላል?

1.7 የጥናቱ አወቃቀር

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አወቃቀር በ አራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን። በምዕራፍ አንድ ምስጋና፣ አጠቃሎ፣ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አብይ አላማ ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች እንዲሁም የጥናቱ አወቃቀር ናቸዉ። ምዕራፍ ሁለት፣ክለሳ ድርሳናት፣የፊልም ምንነት፣የገጸ ባህሪ ምንነት፣የገጸገፀ-ባህሪ አሳሳል ደረጃ ፣ አካላዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ደረጃ፣ማህበራዊ የገፀ-ባህረ አሳሳል ደረጃ፣ስነ-ልቦናዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ደረጃ፣ሞራላዊ የገፀ-ባህር አሳሳል ደረጃ፣የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

ናቸዉ።።ምዕራፍ ሶስት መረጃ ትንተና ፣የፍቅር ጥግ ፊልም ታሪክ ፣የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ ባህርያት አሳሳል፣ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ፣ዋቢ መፅሐፍ ናቸው።።

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዉ በዋናነኝነት ይህንን ጥናት ለመስራት አጥኚዉን የገጠሙት ችግር የጊዜ መጥበብ እና የነግሮች መደራረብ እንዲሁም የምረጃ እጥረት አጋጥሞታል፤ ለምሳሌ ከዚህ በፊት ፊልም ላይ ከገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር ተሰርቶ በቤተመጽሃፍት አለመቀመጡ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጥናቱ ለመስራት ጊዜ ማጣት የመሳሰሉ ናቸዉ።።አጥኚዉ ለገጠሙት ችግሮች የወሰዳቸዉ መፍትሄዎች ከሱ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸዉን ጥናቶች በመመልከት እንዲሁም የትለያዩን ስለፊልም የተጻፉ መጽሃፎችን በማንበብና ጊዜዉን በአግባቡ በመጠቀመ ጥናቱ ሊሰራዉ ችሏል።።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ደርሳናት

2.1 የፊልም ምንነት

አሰልቺ የሆነዉን የሰዉ ልጅ ሂይወታዊ እነቅስቃሴ በሚማርክና ለዛ ባልዉ ጥበባዊ ዉበት አዋዝቶ እና አሳምሮ በምስልና በድምጽ ዉህደት ህበር በማቅረብ ይታወቃል፤ የፊልም ጥበብ። ከላይ የመጽሃፉ የምጀምሪያ ክፍል የጠቀሰዉ የአህዝ መግለጫ የያዘ ጥቅስም በዩ.ኤስም አሜሪካ ዉስጥ ብፊልም ጽህፈ ተዉኔት ጸሃፊነት፤ በመምህርነት እና ተመራማሪነት ስመጥር የሆነዉ ረአይ ፍሬንሻም ስለ ፊልም አጻጻፍ ዘዴ በሚያስተምረዉ teach your sel screen writing በተሰኘዉ መጽሃፍ ዉስጥ በሆሊዉድ የፊልም እንዱስትሪ ዉስጥ ስላለዉ ሂደት ምስክርነት የስጠበት ነዉ። አዲስ ተስፋ "የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ብለሃት" (2005፤vii)

ፊልም በካሜራ አማካኝነት የተቀረፁ የተንቀሳቃሽ ምሰሎች ስብስብ ነው። ፊልም ከመናገር ይልቅ ታሪክ በማሳየት የመንገሪያ ጥበብ ሲሆን ይህ ሲባል ግን በፊልም ዉስጥ ንግግር የለም ወይም አያስፈልግም ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ የተለያዩ የሃገራችን ጸሃፊዎች ስለፊልም ምንነት የገለጿቸዉ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸዉ።

ዘላለም ተፈራ "የፊልም ትወና ጥበብ" በተሰኘዉ መፅሐፍ ላይ ስለ ፊልም ምንነት እንዲህ ሲል ገልጿል "የፊልም ጥበብ በተንቀሳቃሽ ምስሎች አማካኝነት ለተደራሲያን ታሪክን የምንናገርበት፣ ማህበራዊ አኗኗር፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ እና ታሪካዊ ክስተቶችን ለተመልካች የሚያሳይበት ልዩ ጥበብ ነው። የፊልም ምንነት የበለጠ ለመረዳት ከሌሎች የጥበብ ዘርፎች ጋር ያለውን ልዩነት ማየት ጠቃሚ ነው። (2010፣31)

ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው የአዲስ ተስፋ "የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ብለሃት" በተሰኘው መፅሐፍ ላይ ሰለ ፊልም ሀሳብ እንዲህ ሲል ይገልጻል። ፊልም ታሪክን በምስል በድርጊትና በእንቅስቃሴ ቅንብር የመግለጽ እና የመንገር ጥበብ ነው። ታሪክን የተሸከሙት ባለታሪክ የጊዜ እና የቦታ ገደብ ሳይኖርባቸው የሚያስቡትን፣ የሚኖሩትን ፣

የሚያጋጥማቸው ችግርና የሚወጡበት ስልት ለተመልካች ማውራት በቻ ሳይሆን በማሳየት ታሪክ የመንገሪያ መንገድ ነው። (2005፤34)

በሌላ በኩል ደግሞ ሚካኤል ልዑልሰገድ "የፊልም ፅሁፍ አፃፃፍ" በተሰኘው መፅሐፍ ላይ ስለ ፊልም ምንነት እንዲህ ሲል ገልጿል። "ፊልም ከግለሰብ አንስቶ እስከ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ታሪኮች በምስል እና በድምፅ አቀናብሮ በቪዲዮ ወይም በሲኒማ ቤቶች የሚያሳይ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው። " (2010፤18)

2.2 የገፀ-ባህርይ ምንነት

ገጸባህሪ ጸሃፊው ሊተርክ ያሰበውን ታሪክ የሚሸከም ሰዉ፣ እነሰሳ፣ ወይም ሰዉኛ ስበናን የሚላበስ ማንኛዉንም ነገር ይወክላል። የሰዉን በህርይ የሚወክል እንደሰዉ የሚወድቅ እና የሚነሳ ነዉ። ጸሃፊዉ በጥናት የዳበረ ሃሳቡን ለምንገር የሚረዳዉ ታሪኩ የሚሸከምለት የታሪኩ ባለቤት ያስፈልገዋል፣ ምክንያቱም በይትኛዉም የድራማ ጽሁፍ ዉስጥ በጽሁፍ ደረጃ መጀመሪያ ጸሃፊዉ ሊመልሰዉ የሚገባዉ ጥያቄ "ይሄ ታሪክ የማነዉ? የሚለዉን ነዉ። አንድ ጸሃፊ ይዞት የተነሳዉን ሃሳብ በተፈለገዉና በተመረጠዉ ሰአት መጥኖ ለማሳየት የሚፈጥረዉ ገጸባህሪ ሙሉና የታሪኩ ባለቤት ሆኖ፣ ተመልካቹ እያንዳንዱን የታሪክ ዉጣ ወረድ እየተከተለ ያየዉን ዘንድ አሳማኝ በሆነ መንገድ መቀረጽ አለበት።

ገፀ-ባህሪያት የሚባሉት የፈጠራው ዓለም ውስጥ በፀሐፊው የሚፈጠሩ ፍጡራን ናቸው። የምናቡ አለም ፍጡራ በዋነኝነት በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን ሰዎች፣እንሰሳትና ረቂቅ ሃሳቦች ወይም መናፍስት ናቸው።

ገባህሪያ"የታሪባለቤት"የታሪኩ ተሳታፊ በመባል የሚታወቅ ሲሆኑ ስያሜ አላቸው።ገፀ-ባህሪ በጣም ጠቃሚ ከሚባሉት የፊልም አላባውያን ውስጥ አንዱ ነው። ገፀባህርይ የሚባለው ቃል በፈጠራ ታሪክ ውስጥ ያሉትን ድርሰትን ሰዎች (አበበ፣ ከበደ፣ አልማዝ) በድርሰቱ ውስጥ ያሉትን እንሰሳት (አህያ ፣ጅብ፣ በግ፣ ቀበሮ) እረቂቅ ሀሳቦችን (ተንኮል ፣ደግነት፣ መልካም ስራ፣ ቁንጅና የመሳሰሉትን ይወክላል። ገፀ-ባህሪያት በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው፣ ባህሪ ተጎናጽፈው፣ መጠሪያ ተሰጧቸው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው፣ የሚንቀሳቀሱ፣ የሚተነፍ የሚኖሩ፣የሚሞቱ፣ የሚርባቸው፣ የሚጠማቸው የሚያፈቅሩ፣ የሚጠሉ የሚደሰቱ እና የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው። ብሎ ዘሪሁን አስፋው፤ 1992፤1601 ገልፆታል።

2.3 ገፀባህርይ የሚሳሉበት መንገድ

ገጸባህሪያት የሚሳሉት በተለያዩ የገጸባህሪያቱን ሙሉ ማንነት የሚተነተንበት መንገድ ሲሆን የገጸባህሪዉ ስም እንደጸሬዉ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ከታሪኩ ጋር በሚኖረዉ የጠበቀ ቁርኝት የተቀራረብ ወይም የተቃረነ ምክንያታዊ ስም አልያም ለመግባቢያ ብቻ በሚል ቀላል ቢሆን ይመርጣል። አንዳንድ ስያሜዎች ከስያሜዎች ባለቤቶች ጋር በምግባር፣ በአካላዊ፣ ሁኔታ በቁመና የሚጋጩ ሆነዉ የሚገኙበት አጋጣሚ ስላለ ይህንን ልብ በማለት እንድታሪኩ አካሄድ እና ሁናቴ ስም ማዉጣት ያስፈልጋል። የገጸባህሪያትን ያለፈ ታሪክ ማወቅ በገጸባህሪ ስም አሰያየም ሂደት ላይ ሊያበረክተዉ የሚገባ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋጻኦ አለዉ። ምክን ያቱም የስም አወጣጥ ከወላጆችና ከስሙ ባለቤቶች የስጋ ዘመዶች ምኞት ፍላጎት እና አመለካከት ጋር ይገናኛል። ለምሳሌ በጨዋነቱ እና በጥሩነ ስነምግባር የሚታወቀዉን ገጸባህሪ አሸብር የሚል ስም ቢሰጠዉ የስሙ ባለቤት በባህሪዉ የሚወክለዉ ታሪክ ጋር ይጋጫል ማለት ነዉ፤ ይህ ማለት ግን በጥሩ ምግባሩ የሚወደሰዉን ግለሰብ አሸብር ተብሎ መጠራት አይደለም ማለት አይደለም፤ ይልቁን ወላጆቹ ያሳላፏቸዉ ህይወታቸዉ ታሪኮች ለስሙ መነሻ መንሳኤዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የስም አሰጣጥ ሂደት በርካታ አከራካሪ ጉዳዮች ቢኖሩትም የፊልም ጸሃፊ ግን ለገጸባህሪያቱ የሚያወጣቸዉ ስሞች ገጸባህሪያቱ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ እምነትና ፍልስፍና የሚያጸባርቁ ቢሆኑ ይመረጣል። አዲስ ተስፋ (2005፤86)

ገፀ-ባህሪያት በአራት ዋና ዋና የገፀ-ባህሪያት መሳያ መንገድ ይዋቀራሉ፦

- ✓ የገፀ-ባህሪው አካላዊ ማንነት
- ✓ የገፀ-ባህሪው ማህበራዊ ማንነት
- ✓ የገፀ-ባህሪው ስነ-ልቦናዊ ማንነት
- ✓ የገፀ-ባህሪው ግብረ-ገባዊ ማንነት

2.3.1 አካላዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ደረጃ

አንድ ገጸባህሪ በተለይም ዋነኞቹ ገጸባህሪያት በሚቀርጹ ጊዜ መግለጽ ውይም መታውቅ ካለባቸዉ ዋና ዋና የማንነት

መገለጫዎች ዉስጥ አንደኛዉ አካላዊ ማንነታቸዉ ነዉ። በዚህ ግዑዝ በምንኖር ጊዜ አንዳችን ከአንዳችን በቀላሉ የምንለየዉ በአካላዊ አፈጣጠራችን እንደሆነ ሁሉ በረቂቁ

የድርሰት አለምም ደራሲዉ ገጸባህሪያትን በመልካቸዉና በአካላቸዉ ይለያቸዋል አካላዊ የገፀ-ባህሪያት አሳሳልን ስንመለከት ፆታ፣እድሜ፣መጠን፣ቀለም እንዲሁም ጠቅላላ አቋሙን የምንገልፅበት ነዉ። ይህ ማለት አንድን ገፀ-በህሪ አካላዊ ማንነቱን ስንተነትነዉ እያንዳንዱ በአካሉ ላይ የሚታዩትንለምሳሌ፣እድሜውንፆታዉን፣መጠን፣ቁመት፣ክብደት፣ የፀጉርቀለም፣የመሳሰሉትን በዉስጡ ይይዛል። እነዚህ ሁሉብ የገጸባህሪዉን አካላዊ አወቃቀር የሚገልጹልን ሲሆን በተጨማሪም ገጸ-ባህሪው የሚለብሳቸዉ ልብሶች የሚዛቸዉ እቃዎች አብረዉ ሊገለጹ ይችላሉ። አንድ ተዋናይ የተሰጠዉን ገጸባህሪ አካላዊ አወቃቀር በሚገባ ከተረዳና መተንተን ከተቻለ ገጸባህሪዉን ወደራሱ አምጥቶ አካሉን ለገጸባህሪዉ አካል እንዲስማማ ለማድረግ ይቻለዋል። ይህንን ልምድ ለመቅሰም፣ በእለተ ተእለት ህይወታችን የሚገጥሙንን ሰዎች አካላዊ ማንነት ማጤንና መከታተል አልፎም ማጥናትና መለማመድ ጠቃሚ ነው።

2.3.2 ማህበራዊ የገፀ-ባህረ አሳሳል ደረጃ

አንድ ሰባአዊ ፍጡር በምድራዊ ህይወት ቆይታዉ ወቅት የሚያልፍበት የህይወት መልክ ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖረዉ የህይወት መስተጋብር ሁሉ ማህበራዉ ማንነቱን የሚፈጥርበት ሂደት ነዉ። የገጸባህሪ ማህበራዊ ማንነት ወይም የአሳሳል ደረጃ የምንለዉም ገጸባህሪዉ የሚኖርበት ስነጽሁፋዊ አለም ዉስጥ ያለዉ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊ ቤተሰባዊ ነገሮችን ሚናዎችን ሁሉ አካቶ የያዘ ማነነቱ ማለት ነዉ።

ማህበራዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ስንመለከት እንደ ጋብቻ እና ላጤነት ህይወት፣ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማት ያለዉን፣ተሳትፎ፣ ሀብታምና ደህንነትን፣ የሀይማኖት እና ፖለቲካ አቋም፣ የተሰማሩበት የሞያ መስክ፣ ወይ ዘርፍ የመሳሰሉ ይገኙበታል። ይህ ማለት ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ የምንለዉ በዉስጡ ገፀ-ባህሪው ከማህበረሰቡ ጋር ያለዉን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለብታምና ደሃ፣ የመዝናኛ፣ የስራ ሁኔታ፣ መምህር፣ ተማሪ፣ የቤት እመቤት እና ሀይማኖቶች የተመለከተ ኦርቶዶክስ፣ ሙስሊም፣ ፕሮቴስታንት፣ ያገባ፣ ያላገባ፣ በአንድ እድር፣ እቁብ እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ የሚሳተፍ መሆኑን የምንገልፅበት ነዉ። ናቸዉ ብሎ ሳሙኤል “ተስፋዬ የትወና ጥበብ” በተሰኘዉ መስጽሃፉ ላይ ገልጸታል። “(2005፤50-57)”

2.3.3 ስነ-ልቦናዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል

ስነ-ልቦናዊ የገፀ-ባህሪያት አሳሳል ደረጃ የሚያተኩረው የገፀ-ባህረያት ልዩ ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር፣ሰበብ ድርጊቶች በድምሩ ታቅደዉ ለወጪዉ አለም ገልፅ

የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የገፀ-ባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነዉ። ይህ የገፀ-ባህሪያት አሳሳል ደረጃ የሚገልፀዉ በተለምዷዊ ፍላጎት የትነሽነት የመዉደድ፣የመጥላት በተለይም ዉስጣዊ ፍላጎት ጋር የሚገናኝ የስነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን ይይዛል። ይህ ማለት የገፀ-ባህሪያት ዉስጣዊ ፍላጎት፣መሻት፣ፍቅር፣ ጥንካሬ፣ድክመት፣አላማ፣ስሜት አንዲሁም የስነ-ልቦናዊ ክህሎት የመሳሰሉ በዉስጡ እንደሚታይ እና በተለይም ከዉጫዊ ይልቅ በዉስጣዊ ማንነት ላይ እንደሚያተኩር መረዳት ይቻላል።

2.3.4 ግብረ-ገባዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል

ሞራላዊ ማለት አንድን ግለሰብ መሰረት በማድረግ ማህበረሰቡ ያመነበትን ልክ ነዉ ብሎ ወይም አይደለም ካለዉ ነገር ጋር የሚነፃፀርበት ነዉ። ሞራላዊ አሳሳል የገፀ-ባህሪያትን ሞራላዊ ጉዳይ ላይ የሚያወሳ የአሳሳል ደረጃ ሲሆን እንደ ስነ-ልቦና የገፀ-ባህሪ አሳሳል ሁሉ በረቂቅ ሃሳቦች ማለትም ህሊናዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። ይህ ማለት አንድ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የአኗኗር ስልት አለው። አንድ ግለሰብ ደግሞ ማህበረሰቡ ባወጣው ህግ መሰረት እንዲኖር እና ባህሪን በተመለከተ ከማህበረሰቡ ጋር ያለዉን ቁርኝት የምንገልጽበት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

2.5 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

አጥኚው ከዚህ ጥናት ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸው በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎችን ማግኘት ባይችልም ያገኛቸውን ጥናታዊ ፅሁፎች ከጥናቱ ጋር ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት እንደ ናሙናነት ያቀርባል።

"እየሩሳሌም ሙልጌታ 2012 ዓ.ም ሰውነቷ ፊልም ሴት ገፀ-ባህሪያት ፅንሰ ሃሳብ አንፃር" በሚል ርዕሰ ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባችለር ድግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በፊልም ውስጥ ስለ ተሳሉ የሴት ገፀ-ባህሪያት ፅንስ ሃሳብ አንፃር ብቻ ላይ የሚያጠና በመሆኑ ከአጥኚው ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ልዩነት አለው። አንድነቱ ደግሞ ዋናው ጥናታዊ ፅሁፍ በፊልም ላይ የተሰራ ሲሆን እንዲሁም ደግሞ ስለ ገፀ-ባህርይ ስለሚተነትን ነው።

ቤዛዬ ደመላሽ 2013 ዓ.ም አስታራቂ የተሰኘውን የአማርኛ ፊልም "ከገፀ-ባህሪ አሳሳል አንፃር" በሚል ርዕሰ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነ-ሰብ ኮሌጅ የትያትር ጥበባት ት/ክፍል ለአርት ኦፍ ባችለር ድግሪ ማሟያነት ያቀረበችው ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መሰረት ያደረገው ፊልም ላይ ሲሆን ዋናው ጥናታዊ ፅሁፍ በፊልም ላይ የሚያተኩር እና የገፀ-ባህሪያትን ማንነት ስለሚተነትን በዚህ ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ልዩነታቸው ሁለቱም የተለያዩ የፊልም ርዕሰ ላይ በመሰራታቸው፣ እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ ዓ.ም በመሰራታቸው ነው።

ታለማ ደጉ 2013 ዓ.ም "አንሳሮ ፊልም ከዝግጅት አላባውያን እና ከእንስታዊነት እንቤ አንፃር" በሚል ርዕሰ ለወልቂጤ
ዩኒቨርስቲ ለቴያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባችለር ድግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መሰረት ያደረገው ፊልም ላይ ስለሆነ በዚህ ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት አለው።ልዩነቱ ደግሞ ዋናው ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያተኩረው "በፊልም ከዝግጅት አላባውያን እና ከእንስታዊነት እንቤ አንፃር" በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አለው።

ምዕራፍ ሶስት

3. መረጃ ትንተና

3.1 የፍቅር ጥግ ፊልም ታሪክ

በአዲስ አበባ ከተማ ቅንጦት ለምኔ የምትባል ትንሽ ሰፈር አብረሃም ከልጁ ብረሃን ጋር ይኖራል። አብረሃም ጫማ በመስፋት የሚተዳደር ሲሆን ልጁ ብረሃን ተማሪ ናት። ብረሃን ትምህርት መማር የማትወድ ስለሆነች በየጊዜው ከትምህርት ቤት ለመቅረት ምክንያት ትፈጥራለች። ነገር ግን አባቷ በግድ ይሏት ይሄዳል። ጽጌ የተባለች የአብረሃም ጫማ አሰፊ አብረሃምን ስለምትወደዉ ሁሌም ያልተቀደደ ጫማ እያመጣች ታሰፋለች። ነገር ግን እሱን ለማየት እንደምትመጣ አብረሃም እና ብረሃን ያዉቃሉ። ብረሃን ሁሌም አብረሃም ቤተሰቦቹን እንዲያስተዋዉቃት ትጠይቀዋለች አብረሃም ግን ስለዚህ ጉዳይ ስጠይቅ ሁሌም ዉስጡ ይረበሻል እና መንም መልስ አይስጣትም በዚህ ሁሌም ይጣላሉ። አሁንም ስለ እናቱ እና ስለ ቤተሰቡ ስትጠይቅም ይቆጣታል። ብረሃንም አኩርፋዉ ትታዉ ትሄዳለች። አብረሃም የሚወዳትና እስክትመጣ የሚጠብቃት የሚያፈቅራት ሴት ስላለች ጽጌን ለሱ ያላትን ስሜት እንድትተዉ ይንግራታል። ጽጌም እያለቀሰች ትታዉ ትሄዳለች።

ንድ ቀን አብረሃም ብርትኳን ገዝቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ይወድቃል። የሰፈሩ ሰዎችም አንስቶት ወደ ሆስፒታል ይወስዱታል። ለአብረሃም መታከሚያ የሚሆን ገንዘብ የሰፈሩ ወጣቶች ያሰባስቡለታል። ብረሃን ከአብረሃም ጋር ሆስፒታል በመሆን ታሳክመዋለች። በዚ ሰአት አብረሃም ለብረሃን ስለአለፈበት ህይወት እና ስለ ቤተሰቦችቹ ይንግራታል። አብረሃም ለቤተሰቡ ብቸኛ ልጅ ስለሆን ሃብታም ቤተሰቦችሁ በቅንጦት እና በእንክብካቤ ነዉ ያሳድጉት። አብረሃም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ አጊንቶ እዛዉ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይገባል። አብረሃም ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ቬሮኒካ የተባለች ተማሪ ደገት ትስመዋለች ከዛን ጊዜ ጀምሮ ይወዳታል። ከቬሮኒካ እና ከቹቹ ጋር ጓደኛሞች ይሆናሉ። ቬሮኒካ እና ቹቹ የአብረሃምን ጓደኝነት ለጥቅም መጠቀም ጀመሩ ገንዘቡን ይቀበላሉ። አንድ ቀን ቬሮኒካ እና ቹቹ ሰዉ ላይ ጉዳት አድርሶ እንደታሰረ እና ገንዘብ 80 ሺ ብር እንደሚያስፈልግ ትነግረዋለ። አብረሃም ከቤተሰብ ሰርቆ ይሰጣታል። በዚህ ቀን አብረሃም ከቬሮኒካ አብሮ ልመጀመሪያ ጊዜ አብሮ ይተኛሉ ከዛ በኋላ ብረሃን ተረገዝች።

የአብረሃም አባት በአብረሃም መጥፎ ባህሪ ተናዶ አብረሃምን ሲደበድቡት እናቱ ለማገላገል መሃል ትገባልች። በዚህ ሰአት እናቱ ትወድቃለች እነሱ ግን አላዩዋትም ነበር አብረሃም ከቤት ወቶ ይሄዳል። አባቱ ሲመለስ ሞታ ያገኛታል። አብረሃም ከቤት ወቶ ወደ ቬሮኒካ ቤት ሲሄድ ቬሮኒካ እና ቹቹ አብሮ ተኝቶ ስለ ገንዘቡና ስለእቅዳቸዉ ሲያወሩ እና አብረሃምን ለመጠቀሚያ እንዳደረጉት ሲያወሩ ይሰማል። አብረሃምም ገብቶ ካያቸዉ በኋላ ትቷቸዉ ሲሄድ ቹቹ ተከትሎ በድንጋይ ይመታዋል። አብረሃም ጠዋት ሲነቃ ማታ ከወደቀበት አንስቶ ቤት ከማያዉቀዉ ቤት እራሱን ያገኘዋል። አብረሃም ተነስቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ቤት እንደደረሰ ከቤታቸዉ ሰዉ ተሰብስቦ ሲያለቅስ ያያል የእናቱን መሞት ሲያዉቅ ከቤት ሳይግባ ይመለሳል። ከዛ ጊዜ ጀምሮ በጸጸት እንደሚኖር ለልጁ ብረሃን ይነግራታል። አብረሃም ድንገት

በሽታ ተነስቶበት ጸጥ ይላል። ዶክተሮች መጥቶ ያረጋጉታል። ሩቂያ የነአብረሃም ጎሮቤት ስለ አብረሃም እና እናቱ ለሷ ትታ ወደ ጣሊያን እንደሄደች ለብረሃን ትነግራታለች።

አብረሃም በሽታው በሃገር ዉስጥ ታክሞ ለመዳን ብዙ ጊዜ እንደሚወስድ እና በዉጪ ሃገር ደግሞ ብዙ ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ነግረዉት ወደ ቤቱ ይመለሳል። ብረሃን ከትምህርት ቤት እየቀረች ለአብረሃም እና ለሷ የሚበላ ለማግኘት በየ ገቢያዉ እና ወፍጮ ቤት እየዞረች ትፈልጋለች። ከዛን ባገኘችዉ አባቷን ታስታምማለች። አንድ ቀን ግን አብረሃም ትምህርት ቤት ሄዶ ሲያጣት ገቢያ መሃል ቲማቲም ስትለቅም ያገኛታል። በዚህ በጣም ስለተጸጸተ ልጁን ከእአባቱ ጋር ለማኖር አባቱን ለመጠየቅ ይሄዳል። አብረሃም ልጁን ከአባቱ ጋር ከስቀመጠ ብኋላ ለ ወ/ሮ ሩቂያ ከሰፈሩ እና ከአከባቢዉ ርቆ ለልጁ ሲል እንደሄደና ለእሷም ስላደረገችላቸዉ ነገር ሁሉ ምስጋና በወረቀት ጽፎ ይሄዳል። ብረሃን ከአያቷ ጋር መኖር ትጀምራለች። አያቷም ቀስ በቀስ የልጅ ልጁን እየወደዳት ይመጣል። ከብቸኝነቱ ወጥቶ የተሻለና ደስተኛ ህይወት መኖሩን ይጀምራል። አብረሃም በሄደበት ቦታ የቀን ስራ እየ ሰራ መኖር ይጀምራል። ቬሮኒካ ከሄደች ከአስር አመት በኋላ ተመልሳ ልጇን ፈልጋ ተመልሳ መታለች። ትምህርት ቤት በመሄድም አያቷን ተከትላዉ የምትኖርበትን ቬሮኒካ የብረሃንን አያት ለጇን እንድትቀበል ትከለለች። አያቷም የልጅቱ አብረሃም መጥቶ በሱፊት እንዲዳኝ ይግባኝ ያቀርባል። ፍርድ ቤቱም ተለዋጭ ቀጠሮ ይይዛል። የአብረሃም አባት አብረሃምን ያስፈልገዋል። ነገር ግን ሊያገኘዉ አልቻለም። አብረሃም ባለበት አከባቢ ወድቆ ሌሎች ሰዎች ያገኙታል። በዚህ ሰአት ጽጌ ስልክ ተደዉሎላት አብረሃምን ታገኘዋለች። የፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ደርሶ ፍርድ ቤቱ ልጁን ለቬሪኒካ ሊሰጥ ሲል ጽጌ አብረሃምን ይዛዉ ትመጣለች። ፍርድ ቤቱም ባደረገዉ ተለዋጭ ቀን በረሃን ከአብረሃም ጋር እንድትኖር ይወስናል። አብረሃም ከአባቱ ጋር ይታረቃል። አብረሃም እና ጽጌ ይጋባሉ። አብረሃም፣ጽጌና ብረሃን ከአያታቸዉ ቤት አብሮ ይኖራሉ።

3.1 የፍቅር ጥግ ፊልም ገፀ-ባህሪያት አሳሳል

አብረሃም

ሀ. አካላዊ አሳሳል

አብረሃም የፍቅር ጥግ በተሰኘዉ ፊልም ላይ ዋና ገጸባህሪ ሲሆን የፊልሙም ታሪክም በሱ ላይ ይተመሰረተ ነዉ። ከደቂቃ 00፡32 ሰከንድ እስከ 22፡55 ደቂቃና ሰከንድ 47፡09 ደቂቃና ሰከንድ እስከ 1፡52፡40 ሰከንድ ድረስ ባለዉ የፊልሙ ትእይንት ላይ አብረሃም እድሜዉ ከ30_35 ዉስጥ የሚገኝ ነዉ። በዚህ እድሜ አብረሃም የፊት ቀለሙ ቀይ ሲሆን ነገር ግን በችግር ምክንያት ፊቱ ላይ ማዲያት የወጣበት፣ የሰውነትቱ ቅርፅ ከትከሻዉ ጎበጥ ያለ ፀጉሩ የጎፈረ በግራ እና በቀኝ ገባ ገባ ያለ፣ ከላይ አብዛኛውን ጊዜ ሰፋ ያለ ሸሚዝ ከስር ደግሞ ሰፋ ያለ ውሃ ሰማያዊ ቱታ የሚለብስ ወጣት ገፀ-ባህሪ ነው። አብረሃም ብዚህ ወቅት ያለበትን የህይወት ደረጃ ማለትም ድህነቱን፣ ጉዳቱንና ጸጸቱን ልማሳየት ያስችላል። በ 18፡05 ደቂቃና ሰከንድ አብረሃም ሲታመም ይታያል ይህ ህመሙ ለአልጋ ስላበቃዉ እናም ከሆስፒታል ከውጣ ውዲህ ከቦታ ቦታ ሲንቅሳቅስ ትከሻዉ ጎበጥ ብሎ ጸሙ አድጎ 1፡22፡20 ሰከንድ ባለዉ ላይ እናገኝዋለን። በዚህም የአብረሃም የሰዉነት አቋቋም በቀላሉ የገጸባህሪዉን አካላዊ ማንነት፣ያለበትን ስሜት፣ የህይወት ደረጃ መመልከት እንችላለን።

ለ. ማህበራዊ አሳሳል

በ 22፡56 ሰከንድ እስከ 47፡08 ደቂቃና ሰከንድ ባለዉ የፊልሙ ታሪክ አብረሃም ለቤተሰቡ አንድ ልጅ ሲሆን የሃብታም ቤተሰብ ልጅ እና የትምህርት ደረጃዉ ደግሞ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር። ከቤተሰቦቹ ጋረ ከመጣላቱ በፊት ጥሩ የሚባል ግንኙነት ያለው ነበር። ምክንያቱም በ 1፡03፡44 ሰአት፣ደቂቃና ሰከንድ ሰከንድ ላይ አብረሃም ከቤተሰቡ ጋር እየተሳሳቁ አብሮ ሲበሉ በፊልሙ ላይ ይታያል። በ 17፡ 30 ደቂቃና ሰከንድ ላይ አብረሃም ብርትኳን ይዞ ወደ ቤቱ እየሄደ እያለ የሰፈር ጓደኞቹን መንገድ ላይ ሲያገኛቸዉ ብርትኳን ሲሰጣቸዉ ይታያል። ይህ ደግሞ ከጓደኞቹ ጋር መልካም የሚባል ግንኙነት እንዳልዉ ያሳያል። ለዚህም ነዉ አብረሃም ከአከባቢዉ ሰዉ ጋር መልካም የሚባል ግንኙነት ስላለው ጓደኞቹ በታመመ ጊዜ በ 19፡01 ደቂቃ ያከባቢው ሰው ብር በማሰባሰብ ያሳከሙት። ይህ ደግሞ የምንረዳው ከማህበረሰቡ ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት እንዳለው አንዱ ማሳያ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከጎሮቤቶቹም ጥሩ የሚባል ቅርበት አለዉ። ምክንያቱም እማማ ሩቂያ አብረሃም በታመመ

ጊዜ አሳክሞታል እንዲሁም ምግብ እየሰሩ ቤቱ ድረስ ይወስዱልታል ተስፋ እንዳይ ቆርጥም ይመክሩታል፣ ያበረታቱታልም። ባጠቃላይ እማማ ሩቂያ አብረሃምን እንደልጃቸዉ የሚያዩት ይህ ደግሞ አብረሃም ከማህበረሰቡ መልካም ነገር እንዳልው የሚያሳይ ነዉ። ይሁን እንጂ የአብረሃም ከቹቹ ጋር በቬሮኒካ ምክንያት ሲጣሉ ይታያለ ምክንያቱም ቬሮኒካ የቹቹ ፍቅረኛ ናት አብረሃም ደግሞ ወዲታል በዛ የተነሳ ሁለቱም መልካም የሚባል ግኑኝነት የላችዉም የተሳሉበትም መንግድ ትክክል ንዉ። ምክንያቱም ቪሮኒካ የ ቹቹ ፍቅረኛ ሆና ቹቹ ደግሞ አብረማ ሲወዳት ዝም የሚል ቢሆን ኖሮ ምናልባትም የተሳስት አሳሳል ልንለዉ እንችላለን።

ሐ. ስነ-ልቦናዊ አሳሳል

አብርሃም የሰው ጫማ እየሰፋ የሚኖር ሲሆን ቤተሰቦቹን እራሱ በፈጠረው ችግር ቢለያቸውም የነሱን እርዳታ ሳይጠብቅ በጫማ ስራ የሚተዳደር ፣በሰራው ጠንካራ ፣ስራ ወዳድ እና ደንበኞቹን የሚያከብር ገፀ-ባህሪ ነው። አብረሃም በ 08፡33 ደቂቃ ላይ ጫማ ሲሰፋ ይታያል። አብረሃም እራሱን ዝቅ አድርጎ ጫማ መስፋቱ የሱን የስነ ልቦና ጥንካሬ ያሳያል ምክንያቱም እራሱን እና ልጁን ለማኖር ብሎ የሰዉ ጫማ ለመስፋት ማሰቡ ነዉ፤ ይህ ደግሞ እንደ ጠነካራ ጎን ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን ጫማ ለመስፋት ይቀመጥ እንጂ ሲሰፋ ውይም ሲጠርግ አይታይም ይህ ደግሞ ፊልሙን ለሚመለከ ሰዉ ሊያሳምን አይችልም። አብረሃም በስንልቦናዊ አሳስሉ ላይ የተዋጣለት ገጸባህሪ ነዉ፣ ምክንያቱም ህይወቱን ለማሸነፍ ብሎ ቀን ስራ ሲሰራ በ59ኛዉ ደቂቃ ላይ የታያል። ይህ ደግሞ የሱን የስነልቦናዊ አሳሳል ጥንካሬ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል።

መ. ግብረ-ገባዊ

በ 22፡56 ሰአት፣ደቂቃና እስከ 47፡08 ደቂቃና ሰከንድ ባለዉ የፊልም ደቂቃ እና ሰከንድ ላይ አብረሃም በቤተሰቦቹ የሚወደድ፣ ትሁትና በቤተሰቡ የሚከብር ነበር። በ23፡50ደቂቃና ሰከንድ እስከ 25፡43 ደቂቃና ሰከንድ ዉስጥ ይህን እንመለከታለን። በ 29፡00ደቂቃና ሰከንድ እስከ 46 28 ደቂቃና ሰከንድ ባለዉ ፊልም ደቂቃ ላይ አብረሃም የሚያጋጥመዉን የስነምግባር ለዉጥ እናያልን። በቤተሰብም የተጠላ፣ብቬሮኒካ እና ብቹቹ የተናቀ፣በሽንፈት ይተሞላ ገጸባህሪ ሆኖ እናገኘዋልን ለዚህም ምክንያቱም በ 38፡25 ደቂቃና ሰከንድ ላይ አብረሃም ለቬሮኒካ ፍቅሩን በሚግልጽበት ትእይንት ሲሆን ለፍቅሯም ሲል ካባቱ በ 40፡16 ደቂቃና ሰከንድ ብር ሲሰርቅ ይታያል። በ 47፡57 ደቂቃና ሰከንድ ላይ ባለዉ ትእይንት ላይ በቃለ ፊልም ሲገለጽ

አባ

ጎሽ ተመስገን! ተመስገን! ነቃህ ልጄ?

አብረሃም

የት ነዉ ያለሁት? ማነዉ እዚህ ያመጣኝ?

አባ

እኔ ሳገኝህ ልጄ እራሲህን ስተህ ነበር።

አብረሃም

ምን? ምን ሆኜ ነዉ እራሴን የሳትኩት?

አባ

በልጁ ቂም የሚዝ ወላጅ የለም እና የድሮ እምነታቸዉን መልሰዉ ይስጡሃል አይዞህ በል ሂድ።

አብረሃም

እሺ አባ።

ብረሃን

ሀ.አካላዊ

ብረሃን አካላዊ ማንነቷ ፊልሙ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ደቂቃ ድረስ የማይለወጥ ነዉ። አጠር ያለች እድሜዋ ከ10-12 ውስጥ የሚገመት፣ ቀጭን፣ የፊቷ መልክ ጠይም፣ፀጉሯን ሹሩባ የምትሰራ፣ቀጥ ያለ አቋም ያላት፣ስትራመድ የመትፈጥን እንዲሁም ስትናገር የመቸኮል ባህሪ ያላት፣ ትምህርት ቤት ስትሄድ ከላይ ብጫ ሸሚዝ ከስር ቡናማ ቀለም ያለው ቀሚስ የምትለብስ ሲሆን ይህ ደግሞ አካላዊ ማንነቷ በደንብ እንድንረዳ አድርጎናል። ብረሃን አካላዊ ማንነቷ ልጅ መሆኗን በላይ አሳማኝ ሆኖ ተገኝቷል። የፍቅር ጥግ ፊልም ላይ ብረሃን አካላዊ ማንነቷ የተገለጸበት ከ 00፡49 ደቂቃ እስከ 1፡19፡34 ሰአት፣ደቂቃና ሰከንድ ድረስ ያልዉ ትዕይንት ላይ ብረሃን ከአባቷ አብረሃም ጋር የምትኖርበት ጊዜ ሲሆን

በዚህን ወቅት ከላይ ሸሚዝ፣ከስር ቡናማ ቀለም የለዉ ቀሚስ እና ሮዝ ሹራብ በላዩ ላይ ሸንተረር እና ሮዛማ ቀለምያለዉ ሙሉ ልብስ ከታይት ጋር ትለብሳለች፣የጸጉሯም አሰራር ሹሩባ ነዉ፤ገጽባህሪዋ የተሳለችበት መንገድ ከላይ የተጠቀሰውን

አልባሳት ሆነ የጸጉር አሰራር መጠቀም የሚያስችል ሲሆን ነገር ግን ይህ የተሳለችበት መንገድ አንዱ ደካማ ጎን ነዉ።

ምክንያቱም ብረሃን ከአብረሃም ጋር በምትኖርበት ጊዜ የተጠቀመችዉ አልባሳት ሲቀየር አይታይም ይህ ደግሞ የጊዜ

ለዉጥ አላሳየንም። የብረሃን አያት ሃብታም ነዉ ነገር ግን አያቷ ጋር ሲትኖር የምትልብሰዉ ልብስ ሲቀየር አይታይም።

ለ.ማህበራዊ

በረሃን ለአባቷ ብቸኛ ልጅ ነች። ያደገችውም ካባቷ ጋር ሲሆን የሚተዳደሩትም አባቷ የሰው ጫማ እየጠረገና እየሰፋ በሚያገኙት ገቢ ነው። ከአባቷ ጋር ብቻ እንድታድግ ምክንያት የሆናት ቬሮኒካ የምትባለው እናቷ ከሌላኛው ፍቅረኛዋ ጋር ወደ ጣሊያን ሀገር ትታት ስለሄደች ነው። ብረሃን የተሰኘችዉ ገጸባሪ እድሜዋን ያማከለ የትምህርት ደረጃ ላይ የምትገኝ ሲሆን የምትኖርበት ቤት የደሃ
የምንለዉ ሲሆን ይህንንም ፊልሙ ሲጀምር በ 00፡32 እስከ 07፡20 ድረስ ባለዉ ደቂቃ ዉስጥ እናገኘዋለን። ይህም የገጸባህሪዋን ማህበራዊ ማንነት በቀላሉ ለመረዳት ያስችለናል በመጀመሪያዎቹ የፊልሙ ደቂቃ ዉስጥ ከላይ የተጠቀሰዉን ማህበራዊ ማንነቷን ስለሚያሳዉቅ የተሳልችበት የማህበራዊ ሁኔታዋ ነዉ። ነዉ። በቃለ ፊልም ስንመለከት

እማማ ሩቂያ

አብረሃም አንቺን እስኪያገኝሽ ድረስ ህይወቱና ባህሪው አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቶ ነበር።

ብረሃን

አንቺን እስኪያገኝሽ ድረስ፣ የት ነው እኔን ያገኘኝ?

ሐ. ስነ-ልቦናዊ

በረሃን እንደ ህፃንነቷ ሳትሆን አነጋገሯ ልክ እንደ ትልቅ ሰው ነው። በዛላይ ጨዋታ የምትችል ናት፣ ቢሆንም ግን ቶሎ ታኮርፋለች፣ አባቷን በጣም ስለምትወደው ሲያዝን አትወድም ሲያዝን እሷም አብራው ታዝናለች። ብረሃን ብልጥ እና አስተዋይ ልጅ ናት። ብረሃን አባቷ በታመመ ጊዜ ከትምህርት ቤት እየቀረች እሱን እቤት ትታዉ የሚበላ ለማግኘት ስትል ገቢያ ዉስጥ የወዳደቁ ቲማቲሞችን እየለቀመች እሱን ሽጣ በምታገኘዉ ገንዘብ ምግብ ስትገዛ በ 59ኛዉ ደቂቃ ላይ ይታያለ። ብረሃን ስነልቦናዊ ማንነቷ በስነልቦና ደረጃ አንዱ የገጸባህሪዋ የተሳለችበት ጠካራ ጎን ነዉ።

መ. ግብረ-ገባዊ

የብረሃንን ሞራላዊ ማንነት በሚከተለው ደቂቃ እና ትዕይንት ላይ ለመመልከት ያስችላል።የመጀመሪያዉ በ 04፡39 ደቂቃና ሰከንድ አንስቶ እስከ 05፡43 ደቂቃና ሰከንድ ላይ የሚታይ ሞራላዊ ማንነቷ ነዉ። በዚህ ደቂቃ እና ትዕይንት ላይ ብረሃን አንድ ህፃን

ልጅ ከአባቱ ጋረ ማውራት የሌለባትን ስታወራ ትታያለች። ብረሃን መንገድ ላይ አብረሃም ትምህርት ቤት ሊያደርሳት ሲሄድ ከአድ ህጻን የማይጠበቅ ቃላት ትናገረዋለች። ብረሃን የስነ ምግባር ችግር እንዳለባት በፊልሙ ላይ በግልጽ ይታያል ይህም በቃለ ፊልም

አብረሃም

ቦርሳውን ከፍ አዬርገሽ ያዥው እንጂ?

ብረሃን

በራሴ ቦርሳ እደፈለገኝ ቢይዘው ምን አገባህ? ስማ!

አብረሃም

ስማ?

ብረሃን

ደግሞ እኔ በጣም ርቦኛል

አብረሃም

በለአትሽ ተነስተሽ ቁርስሽን መብላት የራሺ ድርሻ ነው።

ብረሃን

በመጀመሪያ ላታበላኝ ማን ውለደኝ አለህ?

ብረሃን

ሀ.አካላዊ

ብረሃን መካከለኛ ቁመት ያለው፣ ትንሽ ቦርጭ ቢጤ ያለችው ጠይም መልክ እና ፊቱ በግራ እና በቀኝ እስከ አገጩ ድረስ በነጭ ፂም የተሞላ እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ መነፅር የሚያደርግ እና ፀጉሩ የተበጠረ ሙሉ ነጭ ፀጉር የበዛበት፣ ከአፍንጫው ስር ነጭ ፂም ያለው፣ የጥርሱ አደራደራቸው የሚማረክ፣ እድሜው በሃምሳዎቹ ውስጥ የሚገመት፣ ሲራመድ ከትከሻዉ ዝቅ ያለ ሸማግሌ ነው። የብረሃን አካላዊ ማንነት በተለያዩ ትዕይንቶች ላይ የታየ ሲሆን በሁሉም ትዕይንት የሱን የእድሜ እና የአካል ለዉጥ የሚያሳይ ነዉ። ምክንያቱም የጸማቸዉ ነጭ መሆን እንዲሁም አካሄዳቸዉ እና አነጋገራቸዉ ትልቅ ሰዉ መሆኑን ይሳያል።

ለ.ማህበራዊ

ብረሃን በማህበራዊ ማንነታቸዉ ሲታይ የአንድ ልጅ አባት ናቸዉ። ቤተሰቦቻቸው ሁሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው። ብረሃን ሁሌም በልጃቸው አብረሃም ምክንያት

በድንገት የሞተችው ባለቤታቸውን ሲያስታውሱ ፎቶዋን እያዩ ያለቅሳሉ። በፊልሙ ላይ እንደታይዉ የብረሃን ማህበራዊ አሳሳል ላይ ከሰፊሩ ስዉ ወይም ከጎሮቤቶቻቸዉ ያላቸዉ ማህበራዊ ግንኙነት ደካማ ሆኖ ተገኝቷል።በቻአዉ እንዲሆን ያደረጋቸዉ የልጃቸዉ አብረሃም ባለቤታቸዉን መግደል ምክንያት ነው። የሚኖሩበት የቤታቸው ጊቢ ሰፊ ዙሪያዉን በግንብ የታጠረ ሲሆን ቤት ውስጥ ያሉት እቃዎችም የተቀናጡና ውድ እንዲሁም ባለቶዮታ መኪና ናቸው።

ብረሃን የተሳለበት ማህበራዊ የገጸባህሪ አሳሳል ከላይ የተጠቀሱ ዋና ዋና ነገሮችን ያሳየን እንጂ ሙሉ የገጸባህሪዉን ማህበራዊ አሳሳል በግልጽ አያሳይም። ለምሳሌ የትምህርት ደረጃዉን፣ የስራ ሁኔታዉን፣የጓደኛዉን ወይም የቅርብ ዘመድ አያሳየንም። ብረሃ በፊልሙ ላይ ብቸኝነትን የመረጡበት ዋናዉ ምክንያት የባለቤታታቸዉ በሚወዱት በልጃቸዉ ምክንያት በሞት ማጣታቸዉ ነዉ።

ሐ. ስነ-ልቦናዊ

የአብረሃምን ስነልቦናዊ ማንነት ከ 23፡51 ደቂቃ ሰከንድና እስከ 44፡27 ደቂቃና ሰከንድ ዉስጥ ብረሃን ለቤተሰቡ ፍቅር ያል ልጁን አብዝቶ የሚወድ ነዉ። ይህንንም በ25፡06 ደቂቃና ሰከንድ ላይ መመልከት እንችላለን። ብረሃን የልጁ ሁኔታ የሚያስጨንቀዉ ይህም በ36፡04 ደቂቃና ሰከንድ እስከ 37፡34 ደቂቃና ሰከንድ ዉስጥ መመልከት እንችላለን። ብረሃን ልጁ አብረሃም ብር እንደሰረቀዉ ሲያዉቅ ልጁን ይመታዋል። ይህም በ43፡50 ደቂቃና ሰከንድ ላይ ይታያል። የልጁንም መጥፎ ድርጊት አምርሮ የሚጠላ አባት ነዉ። የብረሃን ሃዘንም ሆነ የቅስም መሰበር የልጁ አብረሃም የበሃሪ ለዉጥ ምክንያትና አብረሃም ብር በመስረቁ ምክንያት እንደሆነ በ43፡50 ደቂቃና ሰከንድ ላይ ይታያል። ከ 1፡05፡54 ሰአት፣ ደቂቃና ሰከንድ ላይ እስከ 1፡50፡40 ደቂቃና ሰክንድ ላይ ብረሃን ቅስሙ የተሰበረ በአብረሃም ምክንያት የሚውዳትን ሚስቱን ያጣዉ በልጁ አብረሃም ምክንያት ጸጸት ዉስጥ የገባ ገጸባህሪ ነዉ። ይህንንም በ 1፡08፡11 ሰአት፣ደቂቃና ሰከንድ ላይ መመልከት እንችላለን። ብረሃን ስነልቦናዊ ማንነቱ ጥሩ ጎን ነዉ፣ምክንያቱም የስነልባና አሳሳሉ በዉስጡ ብዙ ስሜትን የያዘ ነዉ። ይህም ደግሞ ቀድሞ በተገለጸዉ መሰረት ለመረዳት በሚያስችል መልክ በፊልሙ ላይ እናገኛለን።

መ. ግብረ-ገባዊ

በዚህ ፊልም ላይ የአብረሃም ጥፋት ቅስም የሚሰብር ቢሆንም ፣ ብረሃን አንድ አባት ምንም ያህል በልጁ ቢያዝንበት እንኳ በራሱ ልጅ እንደማይጨክን አሳይቷል። እንዲሁም ደግሞ ይቅር ባይነቱ ለሌላውም የሚያስተምር ሆኖ ተገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ለልጁ አብረሃም ያለውን ፍቅር ያሳየን ገፀ-ባህሪ ነው።

ቬሮኒካ

ሀ.አካላዊ

የቬሮኒካን አካላዊ ማንነት በ 25፡52 ደቂቃና ሰከንድ ላይ ከላይ ነጭ ኮፊያ ያለዉ ሹራብ ከሹራቡ ስር ነጭ ቲሸርት የለበሰች፣ከስር ጂንስ ሱሪ ከጉልበቱ ላይ በሁለቱም በኩል የተቀደደና ነጭ ሸፍን ጫማ አጥልቃለች፣ ጸጉሯን ጠቅልላዉ ለሁለት ከፍላዋለች። በ 1፡29፡27 ሰአት፣ደቂቃና ሰከንድ ላይ ቬሮኒካ በመካከለኛ ቀጥ ያለ ቁመት ያላት፣ መካከልኛ ሰዉነት ያላት ፣ቀይ መልክ እንዲሁም ፀጉሯን ወደ ኋላ የምታስተኛ ጥቁር እረጅም ፀጉር ያላት በሰላሳዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ ሴት ናት።

ለ.ማህበራዊ

ተጫዋች እና ከሰው ጋር ተግባቢ ስትሆን ይህ ደግሞ አብረሃም እንዲወዳት ያደረገው አንዱ ምክነያት ነው። ቬሮኒካ ፍቅረኛ ቢኖራትም ደንገት ከአብረሃም ጋር በተፈጠረው ግኑኝነት አንድ ልጅ ሊኖራት ችሏል። የተማረችና በዩኒቨርስቲ ደረጃ ተምራ የጨረሰች ነች። ቬሮኒካ ቤተሰቦቿን አታውቅም ያደገችውም በማደጎ ቤት ነው

መ. ስነ-ልቦናዊ

ቬሮኒካ ከቹቹ መለየትን ስለማትፈልግ እና ስለምትወደው እያዘነችም ቢሆን የራሷን ህፃን ልጅ ትታ ከሱ ጋር ወደ ጣሊያን ሀገር ሄዳለች። በአንድ በኩል ለፍቅሯ ታማኝነቷን አሳይታለች በሌላ በኩል ደግሞ ህፃን ልጅ ትታ መሄዷ ትክክለኛ እንዳልሆነ ያመለክታል። ይህ እራስ ወዳድ እንደሆነች ያሳየሴት ገፀ-ባህሪ ናት።

ሐ.ግብረ-ገባዊ

ቬሮኒካ በዚህ ፊልም ላይ የተለያዩ ጥፋቶችን ስትሰራ ቆይታለች፣ በመጀመሪያ ደረጃ ያጠፋችው ጥፋት አብረሃምን በማስመሰልና በማልቀስ ብር ትቀበለዋለች፣ አብርሃም ደግሞ ስለሚወዳት ብሩን የሚሰጣት ከቤተሰቦቹ በመስረቅ ሲሆን ለሱ ህሕይወት መበላሸትም ምክንያት እሷ ነች። ሲቀጥል ደግሞ በህፃንነቷ ትታት ወደ ውጪ ሀገር

የሄደችው ልጇን ካደገች ብኋላ መታ የኔ ልጅ ነች ብላ ፍርድ ቤት መቆሟ ነው። በስተመጨረሻ ግን ልጇንም ፍቅረኛዋንም፣የልጇንም አባት ሳታገኝ ብቻዋን ትቀራለች። ስለዚህ ለሰራችው መጥፎ ተግባር መቀጫዋ ለሰራቸችዉ መጥፎ ነገሮች ከሁሉም ሳትሆን ቀርታለች፤ቬሮኒካ ለፍቅረኛዋ ብላ ብዙ ብታደርግም ሊከዳት ችሏል።

ቹቹ

ሀ.አካላዊ

ቹቹ ቀጠን ያለ መካከለኛ ቁመት ያለው እድሜው በሃያዎቹ ውስጥ የሚገኝ ወጣት ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ፀጉሩን አሳጥሮ የሚቆረጥ እና በአለባበሱ ደግሞ ዘናጭ የሚባል አይነት ነው። የቹቹ አካልዊ ማንነት ላይ የተሳለበት መንገድ ከላይ ብተጠቀሰዉ መሰረት ሲሆን ይህ ደግሞ የሱን አካላዊ ማንነት በፊልሙ ላይ የታይ ነዉ።

ለ.ማህበራዊ

ቹቹ ሚስቱ ከሆነችው ቬሮኒካ ጋር የሚኖር ነገር ግን ልጅ ያልወለደ፣ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የነበረዉ ከጊዜ ቡሃላ ግን የኑሮ ደረጃዉን ያሻሻለ የክርስትና እምነት ተከታይ በዩኒቨርስቲ ደረጃ ተምሮ የጨረሰ እና በህይወቱ ውስጥ ደግሞ የራሱን ጥቅም ብቻ የሚፈልግ እራስ ወዳድ፣ ውሸታም እንዲሁም ቅናተኛ ነው። ለዚህም ደግሞ አብረሃም እና ቬሮኒካ ጭፈራ ቤት ውስጥ አብሮ ሲጨፍሩ በመጥፎ አስተያየት
ሲመለከተው ተስተውሏል። አብረሃም እና ቬሮኒካ እንዲለያዩ ትልቁ ምክንያት የቹቹ ተንኮል ነዉ።

መ. ስነ-ልቦናዊ

በዚህ ፊልም ውስጥ ቹቹን ፈጣንነቱን እንመለከታለን ምክንያቱም ከአብረሃምን ጋር ሲገናኙ ብር ለመቀበል ሲያስብ ወዲያውኑ የአብርሃምን ደካማ ጎን ይፈልጋል ከዛን ወዲያውኑ ብር ይቀበለዋለ። ሁሌም ከአብረሃም ጥቅም ይፈልጋል፣ አሱ ግን ምንም ሲያደረግለት አይታይም የአብርሃምን የዋህ መሆን ስለተረዳ ባገኘው ቁጥር ብር የቀበለዋል።

ሐ. ግብረ-ገባዊ

ቸቸ ተንኮለኛ እና ብልጥ ሲሆን፣ እራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ እና ሰው የሚንቅ እንዲሁም ውሸት የሚያበዛ እዲሁም በባህሪው ትዕቢተኛና እልከኛ ወጣት ነው። ከኔ በላይ አዋቂ የለም ብሎ የሚያስብ
ገጸባህሪ ነዉ።

እማማ ሩቂያ

ሀ.አካላዊ

መካከለኛ ቁመት ያላቸው ቀይ ደረበብ ያሉ እድሜያቸው በሃምሳዎቹ መጀመሪያ የሚገኝ የሴት ወይዘሮ ናቸው። እማማ ሩቂያ አብዛኛዉን ጊዜ ጸጉራቸዉ ላይ ቢጫ ፎጣ የሚያስሩ ናቸዉ። ፎጣ ማሰራቸዉ አንድም ሴት እንደመሆናቸዉ የእስልምና እምነት ተከታይ መሆናቸዉን የሚያሳይ ነዉ። ሲቅጥል ድግሞ አብዛኛዉን ጊዜ ፒጃማ የሚለብሱ ሲሆኑ ይህ አለባበሳቸዉ አካላዊ ማንነታቸዉን እንድንረዳ አድርጎናል። ይህ ደግሞ እንደ ጠንካራነን የሚነሳ ነዉ።

ለ.ማህበራዊ

እማማ ሩቂያ የቤት እመቤት ሲሆኑ ባለትዳር ያልሆኑ እና ምንም ልጅ የሌላቸው በጡረታ ገንዘብ የሚተዳደሩ እንዲሁም የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆኑ ጎሮቤታቸው ከሆኑት ከአብረሃም እና የአብርሃም ልጅ ከሆነችው ብረሃን ጋር እንደ ልጃቸው በማየት ጎሮቤታማማቾች ሆነው ተከባብረው አብሮ ይኖራሉ። እማማ ሩቂያ ሙስሊም ቢሆኑም የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድባቸዉ ከሌላዉ ጋር የሚኖሩ ናቸዉ።

መ. ስነ-ልቦናዊ

እማማ ሩቂያ እናትነታቸውን በብዙ መልኩ የሚገልፁ ሩህሩህ አዛኝ ሲሆኑ አብረሃምን እና ብረሃንን ምግብ እየሰሩ የሚያበሉ እዲሁም ሲታመሙ የሚያሳክሙ እናትነታቸውን በደንብ ያሳዩ እናት ናቸው። እማማ ሩቂያ ለራሳቸዉ በአጠረታ ገንዘብ እየኖሩ ለአብረሃም እና ለብረሃን የስጣሉ። ይህን በቃል ፊልም

አብረሃም

ብረሃነዬ መዳኒቱን ልዋጥ?

ብረሃን

ከዛ በፊት እኮ የሆነ ነገር እንድትቀምስ ፊልጌ ነበር።

አብረሃም

እሺ ስጪኝ?

ብረሃን

ግን ቤት ዉስጥ የሚበላ ምንም ነገር የለም

አብረሃም

ሙዝ በዳቦም የለም?

በረሃን

አዎ አልቋል ቆይ ላንተ ለመዳኒት ትንሽ የምትቀምሰዉ ነገር ካለ እማማ ሩቂያን ጠይቂያቸዉ ልምጣ

አብረሃም

አይ ብረሃኔ እሳቸዉስ ኬት ያመጣሉ ለራሳቸዉ የሚያገኟቸዉ የጡረታ ገንዘብ መች በቃቸዉና ነዉ? በዛላይ ሰሞኑን መህዳኒቱን የገዙት እሳቸዉ ናችዉ።

ብረሃን

እና ምን ልስጥህ?

አብረሃም

በቃ እኔ መድሃኒቱን ልዋጥ አንቺ እዛ መሳቢያ ዉስጥ ሃያ ብር አለልሽ ዉሰጂና ሚሪንዳ እና ዳቦ ግዥ

በረሃን

እኔ አንተ ሳትበላ አልበላም

እማማ ሩቂያ

ቤቶች ጥያችውሁ ጠፋዉ አይደል ልጆቼ እንዴት ነህ?

አብረሃም

አረ እማማ ሩቂያ ለኛ ለማድረግ ብሎ እየተቸገሩ እኮ

እማማ ሩቂያ

እየተቸገሩ እኮ ነው? ልቀየምህ ነው አሁንስ አብርሃም ወላሂ እንደዚህ አይባልም ከመቼ ወዲህ ነው አንዲት እናት ልጆቿን ለማብላት ብላ መሞከሯ መቸገር የሆነው? ነው ወይስ አልወለደችኝም ብለህ ነው?

አብረሃም

አረ እኔ እንዳሱ ለማለት አይደለም።

እማማ ሩቂያ

በል አሁን አፉ ብዬሃልዉ ሁለተኛ እንደዚ ያለ ቃል ቢደገም ዋ!

ሐ. ግብረ-ገባዊ

እማማ ሩቂያ በጣም የተከበሩ እና እሳቸውም ሰዎችን አክባሪ ናቸው። ይህንንም የምናየው ቬሮኒካ ብረሃንን ገና በህፃንነቷ ሰታት ወደ ውጪ ሃገር ስትሄድ ምንም ቅር ሳይላት በትህትና እና በክብር ተቀብላ ለአብረሃም ሰታዋለች፣እዚህ ጋር ታማኝነቷንም አሳይታለች። ምክንያቱም እማማ ሩቂያ ልጅ የላቸው የልጅ ፍቅር ስላላቸው የተቀበሉትን ህፃን እራሳቸው ማሳደግ ይችሉ ነበር ነገር ግን ያንን አላደረጉትም ለዛም ነው ታማኝ መሆናቸውን ያየነው።

ፅጌ

ሀ.አካላዊ

ረጅም ቀጠን ያለ ሰውነት ያላት ቀይ መልከመልካም ውበት ያላት፣ እድሜዋ በሃያዎቹ ውስጥ የምትገመት ቀጥ ያለ የሰዉነት ቁመና ያላት እና ሳቂታ ስትሆን አብዛኛውን ጊዜ የቢጃማ ቀሚስ የምትለብስ ወጣት ሴት ገጸባህሪ ናት። ይህንንም ፊልሙን በተምለከትኩ ትዕይንት እና ደቂቃ ላይ መታየት ችያልዉ።

ለ.ማህበራዊ

ፅጌ የላገባች ነገር ግን ከቤተሰብቿ ተለይታ ብቻዋን ከቤተሰብ በምታገኘው ገንዘብ ተከራይታ የምትኖር እንዲሁም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ናት። ምክንያቱም ደግሞ ፊልሙ ላይ ቤተክርስቲያን ስትሄድ ባይታይም በ 15:34 ሰከንድ ላይ አንገቷ ላይ ምስቀል የታያል።

መ. ስነ-ልቦናዊ

ፅጌ የምትወደድ እና የትኛውም ወንድ ለትዳር የሚፈልጋት ወጣት ሴት አይነት ነች። በፊልሙ ላይ አብረሃምን እንደ ምትፈልገው እንዲሁም እንደ ምታፈቅረው እና እሱን ስታይ ደስታ እንደሚሰማት ብትነግረውም እሱ ግን በተቃራኒው እንደሚወዳት፣ ነገር ግን እንደማያፈቅራት እና ከሷ ጋር መሆን እንደማችል ሲነግራት አዘና ትታው ከሄደች ብኋላ ግን እስከ መጨረሻ ተስፋ ሳትቆርጥ ጠብቃው አብረው መሆን ችለዋል። ይህ የሚያሳየው የሷን የመውደድ ጥንካሬና የማፎቀር ጥንካሬ ነው።

ሐ. ግብረ-ገባዊ

ዝምተኛ ስትሆን ደፍራ ስውን የማትናገር አነጋገሯ ትህትና የተሞላበት እራሷን ከፍ ከፍ የማታደርግ ታላቅ እና ታናሿን የምታከብር ሴት ወጣት ናት።

ምዕራፍ አራት

4. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ጽህፍ የፍቅር ጥግ ፊልም ከገጸባህሪያት አሳሳል ደረጃ አንጻር በመተንተን የሚዳስስ ሲሆን በፊልሙ ያሉት ገጸባህሪያት የተሳሉበትን መንገድ በአራቱም የገጸባህሪያት አሳሳል ደረጃ በመተንተን ያስቀምጣል።

በዚህ መሰረት አብረሃም በፊልሙ ላይ እንዴት በገጸባህሪ ደረጃ እንደተሳለ ፊልሙን በመምልከት አካላዊ ማንነቱ መን እነደሆነ፣ ማህበራዊ ሁኔታዉ እነዴት እንደተሳለ፣ በስነ–ልቦና በኩል በምን መልኩ እንደተገነባ እና ግብረ–ገባዊነቷን እንዴት እንደተሳለ በማየት በመተንተን ያስቀምጣል። በተመሳሳይ የብረሃንን ገጸባህሪ አካላዊ ማንነቱ ምን አይነት እንደሆነ፣ ማህበራዊ ሁኔታዋ ምን እንደሆነና በስነልቦና እንዴት እንደተሳለች እና ግብረ–ገባዊ ማንነቷ ምን አይነት ሰዉ እንደሆነች ተተንትኖበታል። የአብረሃም አባት ብረሃን በአካላዊ ገጽታም ምን አይነት እንደሆነ፣ ማህበራዊ ሁኔታዉ ምን እንደሆነና በስነ–ልቦናዊ በኩል እንዴት እንደተሳለ በተጨማሪም ግብረ–ገባዊ ማንነቱ ምን አይነት እንደሆነ ያስቀምጣል። ሌላኛዋ ገጽባህሪ ቬሮኒካ በአካላዊ ማንነቱዋ ምን አይነት እንደሆነች፣ በማህበራዊ ሁኔታዋ ምን አይነት ሴት እንድሆነች፣ በስነልቦናዊ ማነነቷ እና በግብረ–ገባዊ ማንነቷ በገጸባህሪ አሳሳል እንዴት እንደተሳለች በጥልቅት ተተንትናበታለች። በተመሳሳይ ሌሎች ገታጸባህሪያቶች እንደ ደረጃቸዉ በፊልሙ ታሪክ ላይ የተሳሉበት የገጸባህሪ አሳሳል ደረጃዎች በማዉጣት ተተንትኖበታል። በዚህ መሰረት ደራሲዉ ለማህበረሰቡ ቅርብ የሆኑ የሚያዉቃቸዉ፣ የሚመስሏቸዉ ገጸባህሪያትን በመሳል ታአማኒነት ያላቸዉን ገጸባህሪዎች በፊልሙ ላይ ተጠቅሟል። በተጨማሪም አብዛኛዎችን ገጸባህሪያት በአራቱም የገጸባህሪ አሳሳል ድረጃ በጥሩ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ እንደሳላቸዉ ተመልክተናል።

ዋቢ መፅሐፍት

ሚካኤል ልዑልሰገድ። *የፊልም ድርሰት አፃፃፍ* ።አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት፤ (2006) ።

አዲስ ተስፋ። *የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ብለሃት* ።አዲስ አበባ፣ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት፣2005።

ዘሪሁን አስፋው። *የስነ ፅሁፍ መሰረታዊያ።* አዲስ አበባ።ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት ፣1992 ዓ.ም።

ዘላለም ተፈራ። *የፊልም ትወና ጥበብ* ።አዲስ አበባ፤ፋርኢስት ትሬዲንግ፣2010።

ሳሙኤል “ተስፋዬ የትወና ጥበብ” (2010 ዓ.ም) = የትወና ጥበብ = አዲስ አበባ= ሄሪቴጅ ማተሚያ ቤት።